## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

# የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ፈቃድ መመሪያ

ነሀሴ 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ፈቃድ መመሪያ

በሀገራችን የተገነባው የቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተልማት የቀጣይ ትውልድ ኔትወርክ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገና የድምጽ፣ የዳታ እና የምስል አገልግሎቶችን አጣምሮ ለመስጠት ምቹ ሁኔታዎችን የፈጠረ በመሆኑ የቫልዩ አድድ አገልግሎቶችን መስጠት መሠረተልማቱ የሚሰጣቸውን ተጨማሪ አገልግሎቶች በተሟላ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል በመሆኑ፣

በሀገራችን የሞባይል አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እያደገ በመምጣቱ የሞባይል ግንኙነት ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚሰጡ የቫልዩ አድድ አገልግሎቶችን በስፋት ማዳረስና ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚገኘውን አማካይ የገቢ መጠን /Average Revenue per User (ARPU)/ ማሳደግ ለአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት /GDP/ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክት በመሆኑ፣

የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች አቅርቦት ብሄራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዉን ከመሰረታዊ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ጋር በተጨማሪነት ሊሰጡ የሚችሉ የኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን አጣምሮ ለማቅረብ የሚያስችለው በመሆኑ፣

የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ዜጎች የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶችን ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴያቸው እንዲጠቀሙ የሚያስችሉና በመረጃ የበለጸገ ኀብረተሰብን ለመፍጠር እገዛ የሚያደርጉ በመሆኑ፣

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 691/2003 እና በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## አንቀጽ አንድ
## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 3/2003» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## አንቀጽ ሁለት
## ትርጓሜ

በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 (እንደተሻሻለው) እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 47/1991 የተመለከቱት ትርጓሜዎች በዚህ መመሪያ ላይ ተፈጻሚ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ሚኒስቴር"** ማለት የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው።

2. **"ኢትዮ ቴሌኮም"** ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 197/2003 የተቋቋመ ብሄራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ነው።

3. **"መሰረታዊ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት"** ማለት የቴሌፎን፣ የቴሌግራም ወይም የቴሌክስ አገልግሎት ነው።

4. **"የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች"** ማለት መሰረታዊ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ያልሆኑ ወይም በሞባይል፣ በኢንተርኔት ወይም በመደበኛ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚሰጡ ተጨማሪ አገልግሎቶች ናቸው።

5. **"የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ፈቃድ"** ማለት የቫልዩ አድድ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል በዚህ መመሪያ መሰረት በሚኒስቴሩ የተሰጠ ፈቃድ ነው።

6. **"የቫልዩ አድድ አገልግሎት አይነቶች"** ማለት ከዚህ በታች የተጠቀሱት የአገልግሎት አይነቶች ናቸው።

   6.1. **የአጭር መልዕክት አገልግሎት**

   - የአጭር መልዕክት አገልግሎት (SMS))
   - የመለቲሚዲያ መልዕክት አገልግሎት (MMS)
   - በአንድ ጊዜ ለብዙ ሰዎች አጭር መልዕክት የመላክ አገልግሎት
   - የድምጽ መልዕክት አገልግሎት

## 6.2. የክፍያና ገንዘብ ማስተላለፍ አገልግሎት

- የአየር ጊዜ ማጋራት
- የሞባይል የአየር ጊዜ መሙላት
- ክፍያ ወይም ሂሳብ ማሳወቅ
- በሞባይል ገንዘብ ማስተላለፍ

## 6.3. የመዝናኛ እና መረጃ አገልግሎት

- የምስል ስርጭት
- በአገልግሎት ዝርዝር ላይ የተመሠረተ አሳታፊ አቅርቦት
- ለደዋይ የሚሰማ የጥሪ ቶን፡፡
- በሞባይል የሚላኩ ማስታወቂያዎች፡፡
- የጥያቄና መልስ ውድድር ወይም የሚደግፉትን ተወዳዳሪ ማስመረጥ፡፡
- የመረጃ አገልግሎት- ስፖርት፣ ዜና፣ ወቅታዊ ጉዳዮች፣ የአየር ሁኔታ ዘገባ አቅርቦት፡፡

## 6.4. የእንቅስቃሴ ክትትል አገልግሎት

- የመኪና ስምሪት ክትትል፣ የትራንስፖርት ወይም ጭነት ዝውውር አስተዳደር አገልግሎት፣
- የሆቴል፣የሬስቶራንት፣ የገበያ ማዕከል ወዘተ አቅጣጫ መጠቆም አገልግሎት፡፡

## 6.5. የጥሪ ማዕከል አገልግሎት

- አንድ ሰው ራሱ ወይም ሌላ ሰው እየሰራ ስላለው ሥራ ወይም እየሰጠ ስላለው አገልግሎት ለደንበኛ ወይም ደንበኛ ለመሆን ለሚፈልግ ሰው የሚጠቅም መረጃ ደንበኛ ወይም ደንበኛ ለመሆን መረጃ የሚፈልግ ሰው በስልክ ወይም በኢንተርኔት አማካይት ሲጠይቅ መረጃ የሚሰጥበት ወይም በራስ አነሳሽነት የሚላክበት አገልግሎት፡፡

### 6.6. የቨርቹዋል ኢንተርኔት አገልግሎት (Virtual Internet Service)

- ከብሄራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ባንድዊድዝ ወይም የኢንተርኔት ኔትወርክ መሣሪያ በመከራየት ለተጠቃሚዎች የኢንተርኔት አገልግሎት፣ የዌብ ሆስቲንግ አገልግሎት፣ የኢሜል እና ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶችን የመስጠት አገልግሎት።

7. **"ባለፈቃድ"** ማለት የቫልዩ አድድ አገልግሎቶችን ለመስጠት በሚኒስቴሩ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው።

8. **"የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ሰጪ"** ማለት የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ፈቃድ ያለውና ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት የቫልዩ አድድ አገልግሎቶችን የሚሠጥ ሰው ነው።

9. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## አንቀጽ ሶስት
## ስለፈቃድ አስፈላጊነት እና የፈቃዱ ወሰን

1. የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ለመስጠት የሚፈልግ ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማውጣት አለበት።

2. የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ፈቃድ መሰረታዊ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች መስጠትን አይጨምርም።

3. የቫልዩ አድድ አገልግሎት ሰጭዎች የሚሠጧቸው አገልግሎቶች የኢትዮ ቴሌኮም መሰረተልማት ወይም ኔትወርክ ሊሰጥ የሚችላቸውን አገልግሎቶች ነው።

4. የቫልዩ አድድ አገልግሎት ሰጭዎች ለአገልግሎት መስጫ የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎችና ሲስተሞች ማገናኘት የሚችሉት ከኢትዮቴሌኮም መሣሪያዎች፣ ሲስተሞችና መሠረተልማት ጋር ብቻ ነው።

5. የቫልዩ አድድ አገልግሎት ሰጪዎች በሞባይል ክፍያ መፈጸም ወይም ገንዘብ ማስተላለፍ ወይም ሌሎች ከባንክ አገልግሎት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን መስጠት የሚችሉት እነዚህን አገልግሎቶች ለመስጠት ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ፈቃድ ላላቸው ድርጅቶች ብቻ ነው።

6. የቫልዩ አድድ አገልግሎት ሰጪዎች እንደ የምስል ወይም የድምጽ ስርጭት ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራም ወይም የስፖርት ውድድር የቀጥታ ስርጭት የመሳሰሉ

የብሮድካስቲንግ አገልግሎት ይዘት ያላቸው አገልግሎቶችን መስጠት የሚችሉት ከይዘቱ ወይም ከአገልግሎት አቅራቢዎቹ ውክልና ሲኖራቸው እና አገልግሎቱን ለመስጠት ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ፈቃድ ላላቸው ድርጅቶች ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ አራት
## ፈቃድ ለማግኘት የሚያበቁ ሁኔታዎች

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 6 የተጠቀሱትን የቫልዩ አድድ አገልግሎት አይነቶች ለመስጠት የሚያስችል የቫልዩ አድድ አገልገሎት ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

   ሀ/ ሁለት በኤሌክትሪካል ወይም በኮምፒውተር ኢንጂነሪንግ፣ በኮምፒውተር ወይም በኢንፎርሜሽን ሳይንስ፣ ወይም በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ወይም ተመሳሳይ ሙያ በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁና በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች፣

   ለ/ አንድ ከታወቀ የትምህርት ተቋም በኤሌክትሪሲቲ፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወይም በተመሳሳይ ሙያ ዲፕሎማ ያለው ቴክኒሻን፣

   ሐ/ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ራውተሮች፣ ሰርቨሮች እና ሌሎች ተመሳሳይ መሣሪያዎች፣

   መ/ ፈቃዱ የኮልሴንተር አገልግሎት መስጠትን የሚመለከት ከሆነ አንድ አውቶማቲክ የጥሪ ማከፋፈያ እና ሁለት የጥሪ አስተናጋጅ ሠራተኞች

   እንዲኖሩት ያስፈልጋል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ፈቃድ ጠያቂ ሰው፡-

   ሀ/ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 ወይም በኢንቬስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 መሠረት ከሚመለከተው መስሪያ ቤት የምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

   ለ/ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ፣

   ሐ/ የባለሙያዎቹን የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ እና ባለሙያዎቹ ተቀጣሪ ከሆኑ ከድርጅቱ ባለቤት ወይም የንግድ ድርጅት ጋር ያደረጉት የስራ ውል፣

   ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ አምስት
## የፈቃድ ማመልከቻ፣ ፈቃድ ስለመስጠትና ስለመከልከል

1. ማንኛውም አመልካች በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻውን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡

2. አመልካቹ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በሙሉ አሟልቶ ሲያቀርብ ሚኒስቴሩ ፈቃዱን መስጠት አለበት፡፡

3. አመልካቹ በዚህ መመሪያ መሠረት መስፈርቶችን ካላሟላ ሚኒስቴሩ ፈቃዱን ይከለክለዋል፡፡

## አንቀጽ ስድስት
## የፈቃድ ጊዜ፣ ክፍያና ዕድሳት

1. ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ የሚገለግለው በተሠጠበት ጊዜ ላለው አንድ የመንግስት የበጀት ዓመት ሲሆን በየዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ሐምሌ 30 ድረስ ባሉት ቀናት መታደስ አለበት፡፡

2. የቫልዩ አድድ አገልግሎት ፈቃድ ሲወሰድ ብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ/ ለሚኒስቴሩ መከፈል አለበት፡፡

3. የቫልዩ አድድ አገልግሎት ፈቃድ ሲታደስ ብር 10,000 /አስር ሺህ/ ለሚኒስቴሩ መከፈል አለበት፡፡

4. የፈቃድና የእድሳት ክፍያ ዋጋ በሚኒስቴሩ በተለወጠ ጊዜ ክፍያው በአዲሱ የክፍያ ዋጋ መሠረት ይፈጸማል፡፡

## አንቀጽ ሰባት
## በኢትዮ ቴሌኮምና በባለፈቃዱ መካከል ስለሚደረግ ውል

1. የአገልግሎት አቅርቦት እና የአገልግሎት ጥራት ደረጃን የሚወስን ውል በኢትዮ ቴሌኮምና በባለፈቃዱ መካከል መፈረም አለበት፡፡

2. የአገልግሎት አቅርቦትና የአገልግሎት ጥራት ደረጃ ውል ቢያንስ፣

   ሀ/ ኢትዮ ቴሌኮም ለባለፈቃዱ የሚሰጠውን የአገልግሎት አይነትና አገልግሎቱ የሚሰጥበትን የጥራት ደረጃ ጉዳዮችን፣

   ለ/ ብልሽት በሚያጋጥም ጊዜ ቅድሚያ ሰጥቶ በአስቸኳይ ጥገና ስለማድረግና አገልግሎቱ ለሥራ ዝግጁ ስለሚሆንበት ሁኔታና የጊዜ ገደብ፣

ሐ/ በኢትዮ ቴሌኮም ጥፋት በባለፈቃዱ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ስለመካስ የሚመለከቱ ጉዳዮችን፣

መ/ ባለፈቃዱ ከኢትዮ ቴሌኮም ለሚያገኘው አገልግሎት የሚከፍለውን የክፍያ መጠን፣

ሠ/ በኢትዮ ቴሌኮምና በባለፈቃዱ መካከል ስለሚኖር የትርፍ ክፍፍል መጠን፣

ረ/ ስለመረጃ አያያዝና ልውውጥ፣

ሰ/ ስለ መረጃ እና የመረጃ መረብ ደህንነት፣ እና

ሸ/ ውል ሊሰረዝ የሚችልባቸው ሁኔታዎችን

መያዝ አለበት፡፡

3. የአገልግሎት አሰጣጥ ውል በኢትዮ ቴሌኮም በኩል ሊሰረዝ የሚችለው ሚኒስቴሩ የባለፈቃዱን ፈቃድ ከሰረዘ፣ ባለፈቃዱ ለኢትዮ ቴሌኮም ለመክፈል የገባውን የክፍያ ግዴታ በአገልግሎት አሰጣጥ ውል ውስጥ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካልከፈለ፣ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የሚያገናኘውን ወይም በጋራ የሚጠቀምበትን መሣሪያ ሲገለገል ኢትዮ ቴሌኮም ስለደህንነት ያስቀመጣቸውን መመሪያዎች በግልጽ ሁኔታ ከጣሰ፣ ወይም ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ካጋጠመ ብቻ ነው፡፡

4. ባለፈቃዱ ከኢትዮ ቴሌኮም ለሚያገኘው አገልግሎት ክፍያ መፈጸሙን ለማረጋገጥ በአገልግሎት አሰጣጥ ውል ውስጥ የዋስትና ሁኔታ ሊጨመር ይችላል፡፡

## አንቀጽ ስምንት
## የባለፈቃዱ ግዴታዎች

1. ባለፈቃዱ የዚህን መመሪያ እና አግባብነት ያላቸውን ህጎች እና ድንጋጌዎች የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

2. ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ በተሠጠው ፈቃድ መሠረት መስራት የሚችለው በፈቃዱ ላይ የተዘረዘሩትን ስራዎች ብቻ ነው፡፡

3. ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ፈቃዱን ማሳደስ አለበት፡፡

4. ባለፈቃዱ የሚጠቀምባቸዉ መሣሪያዎች ከሚኒስቴሩ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ማግኘት አለባቸው፡፡

5. ባለፈቃዱ የሚጠቀምባቸዉን የቴሌኮሙኒሽን መሳሪያዎች ፈቃድ ለተሰጠዉ አገልግሎት ብቻ ማዋል አለበት፡፡

6. ባለፈቃዱ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያስከፍለውን ዋጋ ለተገልጋዮች በግልጽ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

7. ባለፈቃዱ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ስለሚሰጠው አገልግሎት የኮንትራት ዉል ስምምነት መፈራረም አለበት፡፡

8. ባለፈቃዱ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የአገልግሎት አሰጣጥ ውል ከመፈራረሙ በፊት አገልግሎት የሚሰጥበትን የኔትወርክ ዲዛይን ለኢትዮ ቴሌኮም ማቅረብ አለበት፡፡

9. ባለፈቃዱ ከደንበኞች ጋር የአገልግሎት ውል መፈፀም አለበት፡፡

10. ባለፈቃዱ የኢትዮ ቴሌኮምን የንግድ ስም ወይም ምልክት መጠቀም አይችልም፡፡

11. ባለፈቃዱ ከኢትዮ ቴሌኮም ኔትወርክ ጋር የሚያገናኛቸውን ወይም በጋራ የሚጠቀምባቸውን ማናቸውም መሣሪያዎች ሲገለገል ወይም ስራ ላይ ሲያውል ኢትዮ ቴሌኮም ከደህንነትና ከአደጋ መከላከል ጋር በተያያዘ ያወጣቸውን መመሪያዎች ባከበረ ሁኔታ መሆን አለበት፡፡

12. ባለፈቃዱ ማናቸውንም የመደበኛ ስልክ፣ የሞባይል ወይም የኢንተርኔት ማዞሪያ አገልግሎቶችን ማግኘትና መጠቀም ያለበት ከኢትዮ ቴሌኮም ብቻ ነው፡፡

13. ባለፈቃዱ የማንኛውንም ሰው በቴሌኮሙኒኬሽን ወይም በኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች የሚደረጉ ግንኙነቶች ያለመደፈር መብት የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

14. ባለፈቃዱ የቨርቹዋል ኢንተርኔት አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ሚኒስቴሩ ወይም ኢትዮ ቴሌኮም ወይም ሌላ በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል በስራ ላይ ባዋለው የዶሜይን ስም አሰጣጥ ስርዓት መሰረት የዶሜይን ስም መውሰድ አለበት፡፡

15. ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተጠቀሱ ተመሳሳይ የቫልዩ አድድ አገልግሎት ዓይነቶችን ወይም ፈቃድ ከወሰደባቸው አይነቶች በተጨማሪ አገልግሎት ለመስጠት ሲፈልግ ወይም ፈቃዱን ሲወስድ ያስመዘገባቸው መረጃዎች ሲለወጡ ለሚኒስቴሩ በቅድሚያ ማሳወቅ አለበት፡፡

16. ባለፈቃዱ አገልግሎት መስጠት ሲያቆም ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ እና ፈቃዱን መመለስ አለበት፡፡

17. ባለፈቃዱ ሚኒስቴሩ የመመሪያዉን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ የሚያደርገዉን እንቅስቃሴ የመደገፍና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ
## የኢትዮ ቴሌኮም ግዴታዎች

1. ኢትዮ ቴሌኮም በተመሳሳይ ደረጃ ውስጥ በሚገኙ ባለፈቃዶች መካከል ልዩነት ማድረግ የለበትም፡፡

2. ኢትዮ ቴሌኮም ለቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ፈቃድ ተግባራዊነት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ከባለፈቃዶች ጋር የውል ስምምነት መፈጸም አለበት፡፡

3. ኢትዮ ቴሌኮም ከባለፈቃዶች ጋር በሚፈጽመው የውል ስምምነት ውስጥ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ባለፈቃዱ እንዲፈጽም ከተመለከተው በላይ የከበደ ግዴታ ሊጥልበት አይችልም፡፡

4. ኢትዮ ቴሌኮም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ከባለፈቃዶች ጋር የሚፈጽመው የአገልግሎት አሰጣጥ ውል ረቂቅ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የሚኒስቴሩን ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡

5. ኢትዮ ቴሌኮም ሚኒስቴሩ የዚህን መመሪያ ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ የሚያደርገዉን እንቅስቃሴ የመደገፍና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ አስር
## የሚኒስቴሩ ኃላፊነት

1. ሚኒስቴሩ ይህ መመሪያ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

2. ሚኒስቴሩ ይህ መመሪያ መከበሩን ለማረጋገጥ በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 17 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ባለፈቃዱ አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3. ሚኒስቴሩ በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 /እንደተሻሻለው/ እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 47/1991 ውስጥ የተጠቀሱት የደንበኞች መብት ጥበቃን የሚመለከቱ ጉዳዮችን እንደአግባብነታቸው በዚህ መመሪያ ላይም ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡

4. ሚኒስቴሩ በባለፈቃዶች መካከል ጤናማ የሆነ ውድድር መኖሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

5. ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ግዴታዎች በተላለፉ ባለፈቃዶች ላይ በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 /እንደተሻሻለው/ እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 47/1991 መሠረት እንደአስፈላጊነቱ እርምጃ ይወስዳል፡፡

## አንቀጽ አስራ አንድ
## ክልከላ

1. የቫልዩ አድድ አገልግሎት ሰጪ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን አይነት ይዘት ያላቸው ወይም የሚደግፉ አገልግሎቶችን ማቅረብ፣ መስጠት፣ ማስተላለፍ ወይም ማሰራጨት አይችልም፡-

   ሀ/ ጥላቻን፣ አመጽን ወይም መድልኦን የሚቀሰቅሱ፣

   ለ/ ከሀይማኖት ወይም ከፖለቲካ እምነት ነጻነት ጋር የሚጋጩ፣

   ሐ/ ለህፃናት ወይም እድሜያቸው ከአስራ ስምንት (18) ዓመት በታች ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መተላለፍ የሌለባቸው፣

   መ/ የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችን ማንነት እና እኩልነት መብት የሚጥሱ፣

   ሠ/ በጾታ፣ በጋብቻ፣ በዘር፣ በሀይማኖት፣ በቋንቋ፣ በእድሜ ወይም በአካል ጉዳት ሁኔታ መድልኦን፣ ልዩነትን፣ የበላይነትን ወይም የበታችነትን የሚቀሰቅሱ፣

   ረ/ የህዝብን ደህንነት ፣ ሰላምን፣ ጤናን ፣ትምህርትን ወይም የህዝብን የሞራል ሁኔታ የሚጻረሩ፣

   ሸ/ ወንጀል ለመፈጸም ወይም የተከለከሉ ነገሮችን ለመጠቀም የሚያነሳሱ፣

   ቀ/ የሰው ልጅ ክብርን የሚያዋርዱ፣

   በ/ ተቀባይነት እና አግባብነት የሌለው ወይም ተገቢ የገበያ ውድድርን የማያሰፍን ማስታወቂያ፣

## አንቀጽ አስራ ሁለት
## ፈቃድ ስለመሰረዝ

1. ባለፈቃዱ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8 ወይም በአንቀጽ 11 የተጠቀሱትን ግዴታዎች ወይም ክልከላዎች ካላከበረ፣ ወይም ፈቃዱን ያገኘው በሀሰት ወይም በተጭበረበረ መረጃ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ወይም ከከሰረ ወይም ስራውን ከተወ፣ ወይም ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር የፈረመው የአገልግሎት አሰጣጥ ውል በዚህ መመሪያ መሠረት ከተሰረዘ፣ ወይም ፈቃዱ መታደስ ያለበት ጊዜ ካለፈ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለፈቃድ ከኢትዮ ቴሌኮም የሚያገኘው አገልግሎት እንዲቋረጥበት ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሶስት
## የተሻሩ መመሪዎች

የቫልዩ አድድ አገልግሎቶች ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 2/1997 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

## አንቀጽ አስራ አራት
## መመሪያውን ስለማሻሻል

የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ይህንን መመሪያ የማሻሻል ወይም የመለወጥ ሥልጣን አለው።

## አንቀጽ አስራ አምስት
## መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሀሴ 9 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሀሴ 2 ቀን 2003 ዓ.ም**

**ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል**

**የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትር**